## የ 2003 አዲስ ዓመት በዓል በቶሮንቶ ከተማ በድምቀት ተከብሮ ዋለ፤

## የመኢአድ ድጋፍ በካናዳም በዓሉን በማክበር ተሳታፊ ነበር

በየዓመቱ የሚከበረው የኢትዮጵያውያን ቀንና የአዲስ ዓመት (እንቁጣጣሽ) በዓል ዘንድሮም ቅዳሜ መስከረም 1 ቀን 2003 ዓ/ም በክርስቲ ፓርክ በከፍተኛ ድምቀትና ዝግጅት ተከብሮ ውሏል።

በኢትዮጵያ ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው አማካኝነት ህብረተሰቡን በማስተባበር የሚዘጋጀው ይህ በዓል በየዓመቱ እየተሻሻለና እያደገ የመጣ ሲሆን የዘንድሮዉም የተሳካና የደመቀ በመሆኑ የኢትዮጵያ ማህበር፣ በዝግጅቱ የተሳተፉ ሰራተኞችና የኮሚኒቲው አባሎች ሁሉ ምስጋና ይገባቸዋል።

በበዓሉ ላይ የነጋዴው ህብረተሰብ፣ የተለያዩ የሀይማኖት ተቋማት፣ የሰብዓዊ መብትና የባህል ድርጅቶች፣ የኪነትና አርቲስቶች ተሳትፎ ድምቀትና ውብት ሰጥተውት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንና ካናዳውያን ተገኝተው ህጻናቱ ሲቦርቁና ሲጫወቱ አዛውንቱ በባሕል ልብስ አሸብርቀው እንኳን አደረሳችሁ በመባባል ሰላምታ ሲሰጣጡ የባሕል ዘፈኑ በየቦታው ሲሰማ የቶሮንቶም አየር ሁኔታም ተባባሪ ሁኖ አውድ ዓመቱን አድምቆታል።

እንዳለፈው ዓመትም ዘንድሮም የመኢአድ ድጋፍ በካናዳ ድርጅትም በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያሸበረቀው ድንኳኑ ላይ “እንኳን ለአዲስ ዓመት አደረሳችሁ” በማለት መልካም ምኞቱን በመግለጽ




በጠረጴዛው ላይ ዳቦው ተቆርሶ፣ ፈንድሻው ቀርቦ፣ ቡናው ስኒው ከነረከቦቱ ቀርቦ እጣኑ ጨስ ጨስ እያለ ሲንቧለል፣ በባህል ልብስ ያሸበረቁ እህቶች ቡናው፣ ዳቦው፣ በጎን ደግሞ ጣፋጭ ጥብሱ ቻቻ እያለ ከመጥበሻው እንደወጣ ሲያቀርቡ ወንዶቹ ለህጻናቱም ሀምበርገር እየጠበሱ ሲያቀርቡ ግርግሩ ትርምሱ ሁሉ ያስደስት ነበር።


እንቁጣጣሽ
እንኳን ለአዲስ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ
Happy Ethiopian New Year!






የመኢአድ ደጋፍ በካናዳ አዲሱ ዓመት ለአገራችን ለኢትዮጰያ ሰላም፣ ለሕዝባችን ፍቅርና አንድነትን እድገትን እንዲሰጥልን፤ ሕዝባችንም መብቱንና ነጻነቱን የሚያሰከብርበት አመት እዲሆን ተስፋ እያደረገና እየተመኘ፤ በዚህ ዝግጅት ላይ የተካፈሉትንና የተባበሩትን ሁሉ ከፍተኛ ምሰጋናውን ያቀርባል።

**መልካም አዲስ ዓመት**

መስከረም 1 ቀን 2003